የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም
Coalition for Unity and Democracy Party Support Organisation in UK
(CUDP-SOUK)

## የህዝብን ድምጽ የግል ጥቅም ማራመጃ ማድረግ ታላቅ ክህደት ነው!!!

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የመንግስት ሥልጣን ከህዝብ እንደሚመነጭ፤ ይህም ሥልጣን ነጻና ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ በህዝብ የሚሰጥ ውክልና መሆኑን ያምናል:: ቅንጅት በሚከተለው የፓለቲካ ራዕይ፣ ዓላማውና ተግባሩ ሕዝብ-በህዝብ-ለህዝብ በሚል ጽኑ የዴሞክራሲ እሴት ላይ ተመርኩዞ የህዝብን ልዕልና በማክበር የሚንቀሳቀስና በዚህም የማይናወጽ አቋምና እምነቱ ምክንያት ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል ላይ ያለ ብሄራዊ ድርጅት ነው:: ቅንጅት ከብዙ የፓለቲካ ስብስቦች የሚለይበት መሰረታዊ ጉዳይ ራሱን ለሕዝብ ፍላጎት፣ እምነትና ውሳኔ ፍጹም ተገዥ ማደረጉ መሆኑን በተግባር ያስመሰከረ ከጊዜያዊና ግላዊ ጥቅም ለዘላቂና ማህበራዊ ጥቅም የቆመ ግዙፍ ኃይል መሆኑ ይታመናል::

ቅንጅት በሀገራችን ሰላማዊና ዴሞክራስያዊ የሥልጣን ሽግግር ባህል መዳበር አለበት ብሎ የሚያምንና ለዚህም እምነቱ በሃቅ የታገለና የሚታገል ፓርቲ ነው:: ይህ የማይናወጥ አቅዋም ከዓመት በፊት በተደረገው ምርጫና ከዚያም ተከትሎ የመጣውን ችግር ለመፍታት በተደገው ጥረት ተረጋግጦአል:: ቅንጅት ህዝብን አምኖ ከምርጫ ገብቶአል:: የተከሰቱ ችግሮችም በውይይትና በመግባባት እንዲፈቱ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቶአል:: ወያኔ የሕዝብ ድምጽ በማጭበርበር ራሱን አሸናፊ አድርጎ በማቅረብ ቢውገረገርም፤ ቅንጅት በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ መንገድ ወያኔን በምርጫ ድባቅ የመታው መሆኑ በዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ሳይቀር ተረጋግቶአል:: በምርጫ ካርድ በዝረራ ተሸንፎ ከጨዋታ ውጭ የሆነው ወያኔና አጫፋሪዎቹ እንደሚሉት ይህ ህዝባዊ ድል የተገኘው በገንዘብ ወይም በማጭበርበር ሳይሆን ቅንጅት እንደ ድርጅት ያቀረበው አማራጭ የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ፖሊሲ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን፤ መሪዎቹም ታማኝነትንና አክብሮትን በማግኘታቸው ነው:: ወናፉ ወያኔ ሊያሳምነን እንደሚሞክረው ቅንጅት ድምጽ ያገኘው በጭፍን ጥላቻ ሳይሆን፤ ህዝብ የፓርቲዎቸን የፖሊሲ ልዩነት ተገንዝቦ ጥቅምና ጉዳታቸውን መዝኖ በሰጠው ድምጽ መሆኑ ክብረ-ህሊና ያለው ሰው የሚክደው አይደለም:: ይህን የሚክደው የኢትዮጵያን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ያልተረዳ ጀሌ ወይም የሥርቱ ተጠቃሚና ጋሻ ጃግሬዎቹ ናቸው::

የታሪክ ምጸት ሆኖ በመረጠው ፓርቲ ለመተዳደር እድሉ ቢነፈገውም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጅትን መምረጡ በማያወላውል ሁኔታ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው:: አሸናፊው ተሸናፊ ተብሎ፤ የህዝብ መብትና ድምጽ በጉልበት ተድጦ፣ እንዲመሩ የመረጣቸው መሪዎቹ፤ ከነጻው ፕሬስ አባላትና ከሲቪክ ማህበራት መሪዎች ጋር በጅምላ በዘር ማጥፋት፤ በሀገር ክህደትና በመንግስት ግልበጣ የፈጠራ ወንጀል ተከሰዉ፣ በእስር በመማቀቅ ላይ ናቸው:: ተበዳይ ወንጀለኛ፤ ወንጀለኛው ዳኛ የሆነበት የታሪክ ምጸት ይህ ነው!!.

ጠንካራ ተቃዋሚዎችን በማሰርና በመግደል፤ መንፈሰ ደካማ ግለሰቦቸን በልዩ ልዩ ጥቅም በመደለልና በማስፈራራት፣ በድርጅት ውስጥ ድርጅት በመፍጠር የፖለቲካ ባለጣዎቹን በማጥፋት የተካነው ጎጠኛው ወያኔ፤ «ከፋፍለህ ግዛው» የሚለውን የአምባገነኖች የፖለቲካ ቀመር ተመርኩዞ ሰሞኑን ደግሞ አንዳንድ ከሃዲ የቅንጅት ተመራጮችን አጃቢ ፈረሰኛ አድርጎ ከፊት በማስቀደም የቅንጅትን ህልውና ሊያጠፋ በመንቀሳቀስ ላይ ነው:: የድርጅቱን መሪዎች ለእስር በመዳረግ፣ ቢሮዎቹን በማሸግና ንብረቱን በመዝረፍ የፈጸመው ድርብርብ ግፍ አልበቃ ብሎት ዛሬ ደግሞ ድርጅቱን ከነጭራሹ ለማጥፋት የቅንጅትን የምክር ቤትና የአዲስ አበባ መስተዳድር ተመራጮች ላይ ልዩ ልዩ ተጽዕኖ በማሳደር «አዲሰ ቅንጅት» ለመፍጠር ሰይጣናዊ የተንኮል ሸሩን በማጠዝ ላይ ይገኛል:: ትናንት እንደ ልደቱ አያሌውና ሙሼ ሰሙ የመሳሰሉት ግልብ ግለሰቦችን በመጋለብ አንጃ ፈጥሮ ቅንጅትን

ለማፍረስ ያደረገው ሙከራ የጠበቀውን ያህል ውጤት ባለማምጣቱ የበሸቀው ወያኔ ዛሬ ደግሞ ዳግም ልደቱዎችን ከፊት አሰልፎ ቼ እያለ ድርጅቱን ለማጥፋት ከላይ ታች ማለቱ ድርጅቱን ለማጥፋት ያለውን ምኞት ያሳያል።

የቅንጅት መኖርና አለመኖር በጥቂት ግለሰቦች ፍላጎትና በጎ ፈቀድ የሚወሰን አለመሆኑን እንገነዘባለን። ሆኖም ግና በቅንጅት ስም የተመረጡ ግለሰቦች ክብረ ህሊናቸውን ሸጠውና የተጣለባቸውን አደራ በልተው ለጊዜያዊ ሥልጣንና ቁሳዊ ጥቅም ሲሉ የወያኔ የሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ መሳሪያ መሆናቸው የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን በህዝብ ጥቅምና መብት ላይ ያነጣጠረ ክህደት ነው። ድርጊቱ የሚጎዳው አንድን ድርጅትና የተወሰኑ ግለቦችን ብቻ አይደለም። ድርጊቱ  በሕዝብ ተስፋና በሀገር ላይ የተፈጸ ክህደት መሆኑና ውሎ አድሮም ማስጠየቁ የማይቀር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ይህን የህዝብ ጥቅምና ልዕልና አሳልፎ የሰጠ ክህደትና የፖለቲካ አደርባይነት ማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ በጥብቅ ሊያወግዘውና ሊታገለው ይገባል። ግለሰቦቹ በመውሰድ ላይ ያሉት እርምጃ ለሀገርና ለወገን ህልውናና ክብር ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን በከፈሉ ሰማዕታት ደምና አጥንት ላይ መረማመድ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወድ ልጆች በአደባባይ በጥይት የተቆሉት፤የቅንጅት ከፍተኛ መሪዎችና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባላትና ደጋፊዎች በማጎሪያ ጣቢያዎችና በእስር ቤቶች የሚገረፉት የሚንገላቱትና የሚደበደቡት ወያኔ እንደሚቀላምደው የዘር ማጥፋትና የሀገር ክህደት ወንጀል ፈጽመው ወይም መንግስት ለመገልበጥ አሲረው ሳይሆን ለህዝብ መብትና ውሳኔ የገቡትን ቃል አክብረው በመቆማቸው መሆኑን መዘንጋት አይቻልም። ወያኔን ዴሞክራሲያዊ ጭንብል ለማለብስ በተቋቋመው ምክር ቤት ውስጥ እንዳይገቡ ህዝብ የሰጠውን ውሳኔ አክብረው የህዝብ ድምጽ እንዲከበር ሰላማዊ ትግል ለማድረግ በመቁረጣቸው የታገቱ ጀግኖችን እንደ ተራ ወንጀለኛ ለማስቀጠር መሞዳሞድ የወንጀሉ ተባባሪ ከመሆን አያድንም።

በዚህ ፈታኝ ወቅት በተንበርካኪነት፤ በፍቅረ-ነዋይ ፍላጎት ወይም በሌላ ምክንያት ተለጣፊ ቅንጅት ለመፍጠር የሚደረገው መንቀዥቀዥ በሕዝብ ፍላጎትና መብት ላይ የተቃጣ የፖለቲካ ቁማር በመሆኑ ከወዲሁ ሊገታ ይገባዋል። በፖለቲካ እምነታቸው ብቻ የታሰሩትና የህሊና እስረኛ የሆኑት የቅንጅት መሪዎች ሳይፈቱ ከእነርሱ ውጭ ሌላ አመራር መሰየም በነርሱ ህይወት ላይ መፍረድ፤በህዝብ መብት ማላገጥ አይደለም ብሎ ማሰብ ራስን ማታለል ይሆናል። የድጋፍ ድርጅታችንም የዚህ ዓይነቱን ነገር በጥብቅ ይቃወማል። ጊዜው እነዚህ ብርቅዬ የአገር አውራዎችና የህሊና እሰረኞቹ ከስር እንዲፈቱና ዘረኛው ወያኔ በሕዝብ ላይ የሚያካሂደውን መንግስታዊ ሽብር እንዲያቆም ትግል የሚደረግበት እንጂ፤ለግል ጥቅምና ዝና የሚሯሯጡበት ወቅት አይደለም። ዛሬ በማብረቀረቁ የሚያማለልው ጸዓዳ ወርቅና ቁሳቁስ ነገ በታሪክና በትውልድ ፊት ታጥቦ የማይዳ እድፍ መሆኑን አለመገንዘብ ታላቅ የሞራል ንቅዘትና የፖለቲካ ሞት መሆኑን ማጤን ተገቢ ነው።

ስለሆነም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለጠላት መሳሪያ እየሆኑ ያሉ የቅንጅት ተመራጮች የሚወስዱት እርምጃ ዛሬ በህዝብ ላይ ነገ ደግሞ በራሳቸው ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ በማጤን የድርጅታቸውን ህልውና ለማቆየት መታገል አለባቸው። አሁን ያለው አማራጭ ተንበርካኪነት ሳይሆን፣የኢትዮጵያን ህዝብ ከተጫነበት የአፈና አገዛዝ ተላቆ በመረጣቸው መሪዎቹ ለመተዳደር ያለው ያልተሸራረፈ መብቱ እውን እንዲሆን የተጀመረውን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል በተቀነባበረ መልክ አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ነው። በዚህ ትግል ውስጥ የቅንጅት ተመራጮች ያለባቸውን ድርብ ሃላፊነት በብቃት መወጣት ቢያቅታቸው እንኳ የጠላት ዱላ አቀባይ ከመሆን መታቀብ ይኖርባቸዋል። የሕዝብን ድምጽ የግል ጥቅም ማራመጃ መደረጉ ታሪክና ትውልድ ይቅር የማይሉት ታላቅ ስህተት ይሆናል።

ሰላም፣ ዴሞክራሲና አንድነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ድርጅት በብሪታንያ
ለንደን
ሚያዝያ 1998

መገናኛ ስልክ 07946644831 የፖ.ሳ.ቁጥር 57105 London SW6 2QJ ኢ.ሜል kinjit97@yahoo.co.uk
Contact tel 07946644831 POBox 57105 London SW6 2QJ E-mail kinjit97@yahoo.co.uk